በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ፡-197008

ቀን፡- 05/02/2014 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- ኦዲት ሰርቪስ ኮርፖሬሽን - ጠበቃ መኮንን ይማም ቀረቡ

ተጠሪ ፡- ፀጋ ረታ አስመጪ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ክርክሩ የሽያጭ ውልን መነሻ ያደረገ ሲሆን ጉዳዩ በተጀመረበት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

አመልካች የካቲት 4 ቀን 2011 ዓ.ም ባቀረበው ክስ አመልካች የኮምፒዩተር እቃዎችን ለመግዛት ባወጣው ጨረታ ተጠሪ አሸንፎ እቃዎቹን አቅርቦ ክፍያ የተቀበለ ቢሆንም እቃዎቹን ከሰርቨሩ ጋር የሚያገናኙ ኬብሎችን ባለማቅረቡ ምክንያት እቃዎቹ የተፈለገውን አገልግሎት መስጠት አልቻሉም፡፡ በመሆኑም ኬብሎቹን እንዲያቀርብ ወይም በወቅቱ የገበያ ዋጋ የእቃዎቹን ግምት ብር 182,900 ወጪና ኪሳራን ጨምሮ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ተጠሪ የካቲት 29 ቀን 2011 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች እቃዎቹ ጉድለት ያለባቸው መሆኑን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በ1 አመት ውስጥ ክስ ስላላቀረበ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኗል የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመቃወሚያው ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ ግንኙነታቸው የሽያጭ ውልን መሰረት ያደረገ ስለሆነ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው ስለውሎች በጠቅላላው የተደነገገው የፍ/ሕ/ቁጥር 1845 ሳይሆን የሽያጭ ውልን የሚመለከተው የፍ/ሕ/ቁጥር 2298(1) ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረትም በሻጩ አጭበርባሪነት ካልሆነ በቀር ገዢው ጉድለቱን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በ1 ዓመት ጊዜ ውስጥ ክስ ማቅረብ አለበት፡፡ አመልካች የተጠሪ አጭበርባሪነት ያለበት ስለመሆኑ በክሱ ያልገለፀ ሲሆን ተጠሪው የእቃዎቹን ጉድለት እንዲያስተካክል ያሳወቀው ጥቅምት 7 ቀን 2009 ዓ.ም እንዲሁም ለተረከባቸው እቃዎች ክፍያ የፈጸመው ጥቅምት 25 ቀን 2009 ዓ.ም በመሆኑ ክሱ የቀረበው ሁለት ኣመት ካለፈው በኋላ የካቲት 4 ቀን 2011 ዓ.ም ነው፡፡ የተጠሪ ሰራተኛ ሰኔ 10 ቀን 2009 ዓ.ም UPS 5kg ለቼክአፕ መውሰዱ ጉድለቱን በግልፅ አምኗል አያስብልም፡፡ አምኗል ቢባል እንኳ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በ1 ዓመት ውስጥ ክሱ ስላልቀረበ በይርጋ ይተጋዳል በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡

አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ይግባኙን ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም የስር ፍ/ቤት ውሳኔን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት በማፅናቱ ጥቅምት 13 ቀን 2013 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታውን አቅርቧል፡፡ የአቤቱታው ይዘት ባጭሩ አመልካች በክሱ ላይ ፍሬ ነገርን ከመግለፅ በዘለለ ተጠሪው መቃወሚያ ሊያቀርብ ይችላል ብሎ በማሰብ በክስ መስማት ወቅት ሊያቀርብ የሚችለውን መከራከሪያ አስቀድሞ ማቅረብ ግዴታ በሌለበት ተጠሪው የማታለል እና የማጭበርበር ተግባር ስለመፈፀሙ አመልካች በክሱ አልገለፀም መባሉ ተገቢ አይደለም፡፡ ተጠሪ እቃዎቹን አስተካክላለው ብሎ መውሰዱን አልካደም፡፡ የወሰደውም እቃውን ባስረከበ በአንድ ዓመት ውስጥ ሲሆን እቃውን በእምነት በመውሰድ በተግባር የማታለል እና የማጭበርበር ተግባር የፈፀመ ሲሆን እቃዎቹን አስተካክሎ የሚያቀርብበት ጊዜም ስላልተወሰነ እና እቃዎቹን አስተካክሎ እንዲያስረክብ በተደጋጋሚ በአመልካች ሲጠየቅ ከዛሬ ነገር አስተካክዬ እመልሳለው ማለቱ ስላልተካደ አስፈላጊ ከሆነም ምስክሮቻችንን በመስማት ሊጣራ ሲገባ ክሱ በይርጋ ይታገዳል መባሉ ተገቢ አይደለም፡፡ ውሉ የሽያጭ ብቻ ሳይሆን የጥገና ማደስና መለዋወጫ ማቅረብ መሆኑ በሰነድ ተረጋግጦ እያለ ሽያጭ ብቻ ነው ተብሎ የሽያጭ ሕግ የይርጋ ድንጋጌ ተግባራዊ መደረጉ እንዲሁም እቃው በተጠሪ እጅ ያለ በመሆኑ አመልካች በማንኛውም ጊዜ ንብረቱን መጠየቅ የሚችል ሁኖ እያ ክሱ በይርጋ ይታገዳል መባሉ የፍ/ሕ/ቁጥር 1206 እና የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 63600 ቅፅ 10 የሰጠውን ውሳኔ የሚቃረን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው የሚል ነው፡፡

አቤቱታው በአጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ ተጠሪ የእቃውን ጉድለት አምኖ መልሶ መቀበሉን ለክሱ በሰጠው መልስ አምኖ እያለ ክሱ በአንድ አመት ይርጋ ይታገዳል ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ከፍ/ሕ/ቁጥር

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

2298(1) እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር አገናዝቦ ለመመርመር ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ መልሱን እንዲያቀርብ ታዟል፡፡

ተጠሪም ጥር 10 ቀን 2013 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱ ይዘት ባጭሩ ተጠሪ ለክሱ በአማራጭ በሰጠው መልስ አመልካች የመለሳቸውን እቃዎች አስመልክቶ ክትትል አላደረገም በሚል መቀመጡ አማራጭ ክርክር ከሚሆን በቀር በፍ/ሕ/ቁጥር 1851(ሀ) መሰረት እዳውን አምኗል አያስብልም፡፡ እቃው ጉድለት አለበት በሚል ማሳወቅም ሆነ ጉድለት አለ በሚል እቃ መመለሱ መታመኑ በውጤት ደረጃ አንድ ስለሆነ በፍ/ሕ/ቁጥር 2298(1) መሰረት አመልካች በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ክስ ስላላቀረበ ክሱ በይርጋ ይታገዳል መባሉ ተገቢ መሆኑን የሚገልፅ ነው፡፡

አመልካች የካቲት 1 ቀን 2013 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልሱን ያቀረበ ሲሆን የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን የአመልካች ክስ በይርጋ ይታገዳል ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት በስር ፍ/ቤት ከተደረጉ ክርክሮች፣ በማስረጃ ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች እንዲሁም ለጉዳዩ ተገቢነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካች በዋናነት የሚከራከረው ተጠሪው ክርክር ያስነሳውን እቃ መልሶ መረከቡ እና በተለያዩ ጊዜያትም ከዛሬ ነገ አስተካክዬ አስረክባለው እያለ እንደነበር ባልተካደበት አስፈላጊ ከሆነም ምስክር ሊሰማ ሲገባ እንዲሁም ውሉ ሽያጭ ብቻ ሳይሆን የጥገና እና የመለዋወጫ እቃ አቅርቦት ጭምር ሆኖ እያለ ክሱ በአንድ አመት ይርጋ ይታገዳል መባሉ ተገቢ አይደለም በማለት ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ እቃውን መልሶ መቀበሉን በአማራጭ ክርክር ማቅረቡ እዳውን አምኗል የማያስብል እና አመልካች ጉድለት አለበት በሚል ማሳወቁም ሆነ እቃውን መመለሱ በውጤት ደረጃ ልዩነት ስለሌለው ክሱ በፍ/ሕ/ቁጥር 2298(1) መሰረት በይርጋ ይታገዳል ተብሎ መወሰኑ ተገቢ መሆኑን ገልፆ ተከራክሯል፡፡

ገዢው ክስ ማቅረቡን የከለከለው የሻጩ አጭበርባሪነት ካልሆነ በቀር እቃው እንደ ውሉ ትክክል አለመሆኑን ወይም ጉድለት ያለበት መሆኑን ካስታወቀበት ቀን አንስቶ እስከ አንድ አመት ውስጥ ክስ ያላቀረበ እንደሆነ እቃው ጉድለት አለበት ወይም እንደ ውሉ የቀረበ አይደለም በማለት ክስ ማቅረብ የማይችል መሆኑ በፍ/ሕ/ቁጥር 2298(1) ላይ ተመላክቷል፡፡ ይህም ማለት አንድ ገዢ የገዛው እቃ ላይ ጉድለት ያለበት ከሆነ ጉድለቱ ለሻጩ ባሳወቀ በአንድ አመት ውስጥ ጉድለቱ እንዲስተካከልለት ክስ ካላቀረበ ክሱ በይርጋ ይታገዳል፡፡ ነገር ግን ገዢው በዚህ አንድ አመት ውስጥ ክስ እንዳያቀርብ የሻጩ አጭበርባሪነት ከልክሎት ከሆነ ገዢው ጉድለት መኖሩን ካሳወቀ ከአንድ አመት በኋላም ቢሆን ጉድለቱ እንዲስተካከልለት ክስ ማቅረብ ይችላል፡፡ በሌላ አባባል የሻጩ የማጭበርበር ድርጊት የአንድ አመቱን የይርጋ ጊዜ ገደብ የሚያቋርጥ ምክንያት ይሆናል፡፡ የዚህ ድንጋጌ አላማ ሻጩ በፈጸመው የማጭበርበር ተግባር የወንጀል ድርጊት በመሆኑ በአንድ አመት ውስጥ ክስ አልቀረበም በሚል በወንጀል ድርጊቱ ተጠቃሚ እንዳይሆን ለመከላከል ነው፡፡ ይህ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ማለት ግን የማጭበርበር ድርጊት ከተፈጸመ ምንም አይነት የክስ ማቅረቢያ የጊዜ ገደብ አይኖረውም ማለት አይደለም፡፡ የማጭበርበር ድርጊቱ እንደ ይርጋ ማቋረጫ ጊዜ ተወስዶ የአንድ አመቱ የይርጋ ጊዜ የማጭበርበር ድርጊቱ ከተፈጸመ ጊዜ ጀምሮ እንደአዲስ መቁጠር የሚጀምር ይሆናል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ሌላው መታየት ያለበት የሻጩ አጭበርባሪነት የሚለው አገላለጽ ምን አይነት እና መቼ የሚፈጸም የሻጩን ድርጊት የሚያመለክት ነው? የሚለው ሊሆን ይገባል፡፡ በፍ/ህ/ቁጥር 2297 ሻጩ የሸጠውን ነገር ጉድለቶች ያሉበት መሆኑን ገዢው እንዳያውቃቸው በተንኮል ደብቋቸው ከሆነ ሻጩን ከሀላፊነት የሚያድኑ የውል ቃሎች ቢኖሩ ሻጩ ከተጠያቂነት ማምለጥ እንደማይችል ያመለክታል፡፡ ይህም ማለት ሻጩ ለገዢ በሸጣቸው ነገሮች ላይ ጉድለት መኖሩን እያወቀ በተንኮል በሽያጭ ወቅት ምንም አይነት ጉድለት እንደሌለባቸው አስመስሎ ከሸጠ ወይም ከሽያጭ በኋላም ቢሆን ጉድለቱ እንዳይታወቅ ለማድረግ ሻጩ የማጭበርበር ድርጊት የፈጸመ በመሆኑ ተጠያቂ የማያደርገው የውል ቃል እንኳን ቢኖር ውሉ ተፈጻሚ እንደማይሆን እና ሻጩ በኃላፊነት እንደሚጠየቅ የሚያመለክት ነው፡፡ የፍ/ህ/ቁጥር 2298/1 የፍ/ሕ/ቁጥር 2297 ተከታይ እንደመሆኑ ተጣምረው ሲነበቡ ሻጩ እቃውን ወይም የሚሸጠውን ነገር ለገዢ በሚሸጥበት ወይም በሚያስረክብበት ወቅት እቃው ጉድለት ያለበት መሆኑን እያወቀ ጉድለት እንደሌለ አድርጎ ወይም ጉድለቱ እንዳይታወቅ አድርጎ በማጭበርበር ለገዢ መሸጡ ወይም ማስረከቡ ከተረጋገጠ ክስ የማቅረቢያ ጊዜው በአንድ አመት ይርጋ የማይገደብ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በተቃራኒው ሻጩ በሽያጭ ወይም በርክክብ ወቅት የፈጸመው የማጭበርበር ድርጊት ከሌለ ጉድለቱን ገዢው ለሻጭ ባሳወቀ በአንድ አመት ውስጥ ክስ ካላቀረበ ክሱ በይርጋ ይታገዳል ማለት ነው፡፡

በተያዘው ጉደይ አመልካች ተጠሪው ከዛሬ ነገ እቃውን እጠግናለው በማለት የማጭበርበር ተግባር ስለፈጸመ ክሱ በይርጋ ተቋርጧል መባሉ ተገቢ አይደለም በማለት የሚከራከር ቢሆንም ከላይ እንደተገለጸው በፍ/ሕ/ቁጥር 2298(1) የተገለፀው የማጭበርበር ተግባር እቃውን ከሚመለከት ዝርዝር መግለጫ ወይም በግብይቱ ጊዜ እቃው ጉድለት ያለበት መሆኑ እየታወቀ ይህን በመደበቅ ከተፈጸመ ተግባር ጋር የሚገናኝ ነው፡፡ ተጠሪ ከዛሬ ነገ እቃውን አስተካክላለሁ እያለ ቆይቶ ቢሆን እንኳን ተጠሪ የዋቢነት ሃላፊነቱን አለመወጣቱን የሚያሳይ እንጂ በግዢ ወቅት በእቃው ላይ ያለው ጉድለት በአመልካች እንዳይታወቅ የማጭበርበር ድርጊት መፈጸሙን የሚያመለክት አይደለም፡፡ ከግብይቱ በኋላ የተጠሪ ሰራተኛ ሰኔ 10 ቀን 2009 ዓ.ም UPS 5kg ለቼክአፕ መውሰዱ ጉድለቱን በግልፅ አምኗል የሚያስብል ካለመሆኑም በላይ ተጠሪ ጉድለቱን ለማስተካከል እቃውን ተቀብሏል ቢባል እንኳ በዚህ አግባብ ባለማስተካከሉ አመልካች ተጠሪ እቃውን ለማስተካከል ከተቀበለበት ጊዜ ጀምሮ በሕግ በተገለፀው አንድ አመት ጊዜ ውስጥ ክስ በመመስረት ዳኝነት ሊጠይቅ ይገባ ነበር፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ አመልካች ተጠሪው ከዛሬ ነገ እቃውን አስተካክላለው በማለት ያጭበረበረኝ ስለመሆኑ ምስክሮቼ መሰማት ነበረባቸው በማለት የሚከራከር ቢሆንም በፍትሐብሄር ክርክር ማስረጃ የሚሰማው እና ፍሬ ነገር እንዲነጥር የሚደረገው ለጉዳዩ አወሳሰን የግድ አስፈላጊ ሲሆን ብቻ ስለመሆኑ ከፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም አመልካች ምስክሮቼ ሊሰሙ ይገባ ነበር በማለት የሚያቀርበው ቅሬታ ተገቢነት የለውም፡፡

ማሳታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በመጨረሻም አመልካች ለክሱ መነሻ ያደረገው የገዛዋቸው እቃዎች በውሉ መሰረት ተሟልተው የቀረቡ ባለመሆኑ ተገቢውን አገልግሎት መስጠት አልቻሉም የሚል ሁኖ እያለ እና ውላችን የጥገና እና የመለዋወጫ አቅርቦትን ስለሚጨምር የፍ/ሕ/ቁጥር 2298 ለጉዳዩ ተፈጻሚነት የለውም በማለት የሚያነሳው መከራከሪያ ተገቢነት ስንመለከት አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረበው ክስ ተጠሪው ጥገና እንዲያደርግልኝ ይወሰንልኝ የሚል ግልጽ ዳኝነት አልጠየቀም፡፡ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ከመለዋወጫ እና ጥገና ውል ጋር የተያያዘ ክስ ባላቀረበበት የተጠቀሰው የይርጋ ድንጋጌ ተፈጻሚ ሊሆን አይገባም በሚል የሚያቀርበው መከራከሪያ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ክስ ያቀረበው የሽያጭ ውልን መሰረት አድርጎ በተሸጠው እቃላይ አለ የሚለው ጉድለት በገንዘብ ወይንም በአይነት እንዲስተካከልለት በመሆኑ ለጉዳዩ የፍ/ሕ/ቁጥር 2298/1 ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

በመሆኑም አመልካች ተጠሪ እቃውን እንዲያስተካክል ያሳወቀው ጥቅምት 7 ቀን 2009 ዓ.ም መሆኑ እና ክሱ የቀረበው የካቲት 1 ቀን 2011 ዓ.ም መሆኑ ተረጋግጦ በይርጋ ይታገዳል ተብሎ በስር ፍ/ቤቶች በተሰጠው ብይን ላይ እና ብይኑን በማጽናት በተሰጠው ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁጥር 65181 ግንቦት 16 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ብይን እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 239590 ሐምሌ 22 ቀን 2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት ሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የራሳቸውን ይቻሉ፡፡
3. አመልካች ለተጠሪ እንዲስተካከል ሰጥቻለሁ የሚለውን እቃ በተመለከተ ባለበት ሁኔታ ለማስመለስ ክስ ከማቅረብ ይህ ውሳኔ አያግደውም፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ሄ/መ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም